የበረሃ አባቶች ምክሮች



ጎረቤቶውን ጨምሮ ወደ እንግሊዝኛ የተረጎሙት
ሲስተር ቤኔዲክታ ዋርድ

እንግሊዘኛውን ጨምሮ ወደ አማርኛ የተረጎሙት
አያሌው ዘኢየሱስ
በኔ ፳፻፫ ዓ.ም.
አዲስ አበባ

የበረሃ አባቶች ምክሮች

ዓረብኛውን ጽሑፍ ወደ እንግሊዘኛ የተረጎመችው፡-
ሲስተር ቤኔዲክታ ዋርድ

እንግሊዘኛውን ጽሑፍ ወደ አማርኛ የተረጎመው፡-
አያሌው ዘሊየሱስ

የሽፋን ስዕል፡- ከእንግሊዘኛው መጽሐፍ ሽፋን እንደተወሰደ

ሰኔ 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ከተርጓሚው

ይህችን አነስተኛ ነገር ግን ታላቅ መጽሐፍ የተረጎምኋት በግንቦት ወር መግቢያ 1999 ዓ.ም. ነው። ይሁን እንጂ በቀጣዩ በሰኔ ወር 1999 ዓ.ም. አስቀድሜ «የባሕታውያን አባቶች ሕይወትና የመዝሙራት ተመስጦ» የሚለውን ሦስት በአንድ መጽሐፍ ማተሚያ ቤት ሳስገባ ይህች መጽሐፍ በጠቀስሁት መጽሐፍ ውስጥ ከተረጎምኋቸው ሦስት መጽሐፍ ጋር እንደ አራተኛ መጽሐፍ ለብቻዋ አሳትሜ አወጣታለሁ ብዬ ባስብም በወቅቱ በተለያዩ ምክንያቶች ሳላሳትማት ቀረች። ሳትታተም መቅረት ብቻ አይደለም መተርጎሚንም አስከነጭራሹ ዘነጋሁት።

አሁን በቅርቡ ግን በሲ.ዲ. ጠብቂ ካስቀመጥኋቸው የቀድሞ መጻሕፍቶቼ መካከል አንደኛውን ፈልጌ በመክፈት ያስፈለገኝን መጽሐፍ ከዝርዝሩ ውስጥ ስመርጥ የዚህችን መጽሐፍ የተዘነጋ ፋይል አገኘሁት። በመሆኑም አሁን በመተርጎም ላይ ያለሁትን መጽሐፍ ለጊዜው በማቆም በሁለት ቀን ውስጥ ለኅትመት አዘጋጀሁት። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር እንድትታተም የፈቀደበት ጊዜ አሁን ነው አልሁና አሁን (በመጋቢት ወር 2003 ዓ.ም.) ሦስት በአንድ እና ሁለት በአንድ ሆነው ወደ ማተሚያ ቤት ከሚገቡት አምስት መንፈሳዊ መጻሕፍት ጋር ብቸኛ ስድስተኛ መጽሐፍ ሆና እንድትገባ አደረግሁ፤እኔ አገኘሁ ወይም አዘጋጀሁ ወይም አደርግሁ ልበል እንጂ ሁሉንም በጎ ነገር ያደረገውና የሚያደርገው የሁላችን አምላክና መድኃኒት የሆነው የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

«የበረሃ አባቶች ምክሮች» በማለት የተረጎምኋት የዚህች መንፈሳዊ መጽሐፍ እንግሊዘኛ ርዕስ «The Sayings of the Desert Fathers.» ነው የሚለው። እኔ የመጽሐፏን ርዕስ «የበረሃ አባቶች አባባሎች ወይም ብሒሎች» ብዬ ከመተርጎም ይልቅ «የበረሃ አባቶች ምክሮች» ብዬ የተረጎምኋት «ምክሮች» የሚለው ቃል ቀደም ብዬ ከጠቀስኋቸው ሁለት ቃላት የተሻለ ሆኖ ስላገኘሁትና ብዙዎቹ አባቶች እነዚህን ቃላት ሊደቀ መዛሙርቶቻቸው ያስተላለፏቸው በምክር መልክ ስለ ነበረ ነው። መጽሐፉን በትርጉም (ከዓረብኛ ወደ እንግሊዘኛ) ያዘጋጀችው ሲስተር ቤኔዲክታ ዋርድ (Sister Benedicta Ward) ናት። እንደ ተጠቀሱት አባቶች ቁጥር መጽሐፉ በስምንት ምዕራፍ የተከፋፈለ ነው።

በዚህች መጽሐፍ ውስጥ እጅግ ድንቅ የሆኑ የስምንት ዋና ዋና የበረሃ መነኮሳት አባቶች ምክሮች ተገልጠዋል። እያንዳንዱ የበረሃ አባት ያሉት ከ4 እስከ 24 የሚደርሱ ምክሮች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተካተዋል። እንዱ የበረሃ መነኩሴ የሌላው የበረሃ መነኩሴ አባት ሲሆን ሌላው ደግሞ የእርሱ ረድዕ ነው፤አንደኛው በረኸም ጸሎቱ ሲታወቅ ሌላው ደግሞ ርኩሳን መናፍስትን በማባረሩ ይታወቃል፤አንዱ በበዛ ትሕትናው ሲታወቅ ሌላኛው ደግሞ በአርምሞው ይታወቃል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ መንፈስ ቅዱስ አንድ ሆኖ ለእነዚህ የበረሃ መነኮሳት አባቶች የሰጠው ስጦታ የተለያየ ነው፤1ኛ ቆሮ 12:4-11። ሁሉም ግን በእምነት ጽናታቸው፣ በጸሎት ብርታታቸው፣ በዲያብሎስ በመፈተናቸው፣ ያላቸውን ሁሉ በዓለም ውስጥ ትተው ወደ ምድረ በዳ በመውጣታቸውና ያለ ምግብ ለረኸም ለዓታት መቆየት በመቻላቸው. . . ወዘተ ይመሰከሩለሉ።

መጽሐፉ ቀጣይ የሕይወት ዘመናቸውን በዓለም ውስጥ ያላቸውን ሀብትና ንብረት በመሸጥ ክርስቶስን ለመከተል ለወጡና ለሚወጡ አባቶች፣ እናቶች፣ ወንድሞችና እኅቶች ወገኖቼ ታላቅ የምንኩስና ትምህርትና መመሪያ ይሰጣል ብዬ አምናለሁ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሮርቁናስ ማዶ ላገኘው ኀብዝ «. . . ፍጹም ልትሆን ብትወድ፤ሂድና ያለህን ሽጠህ ለድሆች ስጥ፤መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፤መጥተህም ተከተለኝ. . .» (ማቴ 19:21) ብሎ መናገሩ በዓለም ውስጥ ፍጹም ሆኖ መኖር፣ ከዓለም የተገኘውን ለዓለም መልሶ መሸጥ፣ የሸጡትን ለድሆች መስጠትና በሰማያት መዝገብ ለማግኘት እርሱን መከተል የሚቻል ሰማያዊ ሕይወት መሆኑን አረጋግጠልናል። እንደ ኀብዙ በዓለም ውስጥ ብዙ ሀብት ያፈሩና ለማፍራት የሚፈልጉ ምድራውያን ሰዎች ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ለድሆች ለመስጠት አይደለም ካላቸው ላይ ከፍለው ለድሆችና ለቤተ ክርስቲያን ለመስጠት ሲያቅታቸው የምንኩስናን ሕይወት በቤተ ክርስቲያን ውስጥና በመናፍቃን አዳራሽ ለመንቀፍ መሰብሰብ ግን ጥፋት ነው፤ይህ ሕይወት የእቢዩ ኤልያስ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ፣ የአባ እንጦንስ፣. . . እና የሌሎችም ቅዱሳን አባቶች ሕይወት ነውና። ይቆየን።

አያሌው ዘሊየሱስ

ጎንር 10 ቀን 2003 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ምስጋና

- የትርጉሙን ረቂቅ ውድ ጊዜውን መሥዋዕት በማድረግ አንብቦ ገንቢ አስተያየቱን ለሰጠኝ ለዲያቆን ሲራክ ዘኢየሱስ፤
- እተረጉመው ዘንድ የእንግሊዘኛውን መጽሐፍ ለሰጠኝ ወንድሜ ለታዬምስ ግዛቸው፤
- መጽሐፉ ተተርጉሞ እንዲወጣ በተለያየ መንገድ ለረዳችኝ እኅቴ ለዕሌኒ በርሔ እና ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ መንፈሳዊ ምስጋናዬን አቅርቤላቸዋለሁ::

የመጽሐፉ የእንግሊዘኛ ርዕስ:- *"The Sayings of the Desert Fathers."*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን
ደንብና ሥርዓት ጠብቆ የተዘጋጀ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

አድራሻ:- ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
ወይም
በስልክ ቁጥሮች:- 0911 15 75 96፤0911 61 59 15

❖ ከተርጓሚው 3

❖ ማውጫ 5

❖ ምርጥ የበረሃ አባቶች ምክሮች 6

❖ ታላቁ አባ እንጦንስ 7
(ABBA ANTHONY THE GREAT)

❖ አባ አርሳኔምስ 23
(ABBA ARSENIUS)

❖ አባ ዳንኤል 35
(ABBA DANIEL)

❖ አባ ዮሐንስ አጭሩ (ዮሐንስ ሐጺር) 39
(ABBA JOHN THE DWRAF)

❖ ካህኑ አባ ኤሲዶር (ኤስድሮስ). 54
(ABBA ISIDORE THE PRIEST)

❖ ታላቁ አባ መቃርስ 58
(ABBA MACARIUS THE GREAT)

❖ ጥቁሩ አባ ሙሴ (ሙሴ ጸሊም) 85
(ABBA MOSES THE NEGRO)

❖ አባ ሰራጵዮን 94
(ABBA SERAPION)

❖ በተርጓሚው የተተረጎሙና የተዘጋጁ መጻሕፍት ዝርዝር 99

❖ ስለ መጽሐፉ አጭር መግለጫ በእንግሊዘኛ ቋንቋ . . 100

ታላቁ አባ እንጦንስ

(ABBA ANTHONY THE GREAT)

«የመነኮሳት አባት» ተብሎ የሚጠራው ታላቁ እንጦንስ በማዕከላዊ ግብፅ ውስጥ በግብርና ሥራ ከሚተዳደሩ ክርስቲያን ቤተሰቦች ተወለደ። በ269 ዓ.ም. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥና ተከተለኝ» የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሲነበብ ስለ ሰማ ቃሉን በእርሱ ሕይወት ተግባራዊ አደረገው። ከዚህ በኋላ በሚኖርበት መንደር አካባቢ በሚኖር አንድ ባሕታዊ በመመራት የምናኔውን ሕይወት ጀመረ። በ285 ዓ.ም. ብቻውን ወደ ምድረ በዳ ሄዶ ምናኔውን ተያያዘው። ዝናው በሚኖርበት አቅራቢያ ሠፍረው የሚኖሩትን ሰዎች ስለ ሳበ በ305 ዓ.ም. ለሰዎቹ መንፈሳዊ አባት ይሆናቸው ዘንድ ከበአቱ ወጣ። ከአምስት ዓመታት በኋላ ተመልሶ ወደ ብቸኝነት ሕይወቱ ገባ። በሕይወት ሳለ እስከንድርያን የተመለከታት ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። የመጀመሪያው ክርስቲያኖች በሞት የተቀጡ ጊዜ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጳጳሱ አትናቴዎስ ኑፋቄን ለመቃወም ሲነሣ እርሱን ለማገዝ ወደዚያው የወጣ ጊዜ ነበር። ሲሞት ዕድሜው አንድ መቶ አምስት ዓመት ነበር። የአባ እንጦስ የሕይወት ታሪክ የተጻፈው በቅዱስ አትናቴዎስ ሲሆን ይህ ታሪኩ በክርስቲያኑ ዓለም

ውስጥ የምንከብናን ሕይወት ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል።

1/ ቅዱሱ አባ እንጦንስ በገዳም ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ ብዛት ባላቸው የኃጢአት አሳቦች ይጠቃ ነበር። ስለሆነም በአንድ ወቅት ጥያቄውን ለእግዚአብሔር እንዲህ በማለት ያቀርባል፦

«ጌታዬ ሆይ! እኔ ልድን አወዳለሁ፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ክፋ አሳቦች ሊተዉኝ አልቻሉም። በመከራ ውስጥ ሰሆን ምን ባደርግ ነው የሚሻለኝ? እንዴትስ እድናለሁ?»

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተነሥቶ ወደ ውጪ ሊወጣ ሲል አንድ አርሱን የሚመስል ሰው ቁጭ ብሎ ሥጋጃ ሲሠራ ይመለከታል። ያ ሰው ጥቂት ከሠራ በኋላ ሥራውን አቋርጦ ይነሣና መጸለይ ይጀምራል። ጸሎቱን እንደ ጨረሰም ተመልሶ ሰሌን መታታቱን ይቀጥላል። እንደገና ተነሥቶ ደግሞ ይጸልያል። በዚያን ወቅት ይህን ሁሉ ያደረገው የእግዚአብሔር መልአክ ሲሆን ምክንያቱም አባ እንጦስን ሊያርመውና ሊያስተምረው ፈልጎ ነው።

በመጨረሻ መልአኩ «እንደዚህ ካደረግህ ትድናለህ!» ይለዋል።

አባ እንጦንስ እነዚህን ቃላት ሲሰማ እጅግ ከመደሰቱም በላይ ድፈረትን ይጎናጸፋል። ከዚህ በኋላ አድርግ የተባለውን ስላደረገ ሊድን ችሏል።

2/ ይኸው አባ እንጦንስ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ ሲያሰላስል ከቆየ በኋላ አምላኩን እንዲህ በማለት መጠየቅ ይጀምራል፡-

«ጌታዬ ሆይ! አንዳንድ ሰዎች ገና ልጅ እንዳሉ የሚሞቱትና ሌሎቹ ደግሞ ከመጠን በላይ እስኪያረጁ ድረስ የሚቆዩት ለምንድር ነው? አንዱ ድሀ ሌላው ደግሞ ባለ ጠጋ የሚሆነውስ ስለ ምን ነው? ኃጢአተኞች የሚበለጽጉበትና እውነተኞች የሚያጡበት ምክንያትስ ምንድር ነው?»

ከዚህ በኋላ አንድ ድምፅ «እንጦንስ ሆይ! ትኩረትህን ወደ ራስህ አድርግ! እነዚህ ሁሉ ሊሆኑ የቻሉት እንደ እግዚአብሔር የፍርድ አሠራር ነው። ስለ እነርሱ ታውቅ ዘንድ ለአንተ የተሰጠህ ነገር የለም!» በማለት ሲናገረው አደመጠ።

3/ በአንድ ወቅት ደግሞ አንድ ሰው አባ እንጦስን «አንድ ሰው እግዚአብሔርን ያስደስት ዘንድ ምን ማድረግ ይገባዋል?» በማለት ይጠይቀዋል።

አባ እንጦንስ፡- «የምንግርህን በጥንቃቄ አድምጠኝ! አንተ ማንም ብትሆን እግዚአብሔርን በፊትህ አኑር! የምታደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ትእዛዝ አድርጋቸው! የምትኖርበትን ቦታ እንዲሁ በዋዛ ቀይረህ አትሂድ! እነዚህን ሦስት ነገሮች በትክክል የምታደርግ ከሆነ ትድናለህ።» ብሎ መልስ ሰጠው።

4ኛ/ አባ እንጦንስ ለአባ ጴሚን (Poemen) እንዲህ ብሎት ነበር፡- «ምንጊዜም ቢሆን ስለ ኃጢአቶቹ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን የሚወቅስና ፈተናን እስከ ሕይወቱ የመጨረሻ እስትንፋስ ድረስ የሚጠባበቅ ሰው ሥራው ታላቅ ሥራ ነው።»

5ኛ/ እንዲህም ብሏል፡- «በፈተና ያልተፈተነ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።» ቀጠል አድርጎም «ያለ ፈተና ማንም አይድንም!» በማለት ተናግሯል።

6ኛ/ አባ ፓምቦ (Pambo) አባ እንጦስን «ማድረግ ያለብኝ ምንድር ነው?» ብሎ ሲጠይቀው፡-

እንዲህ በማለት መልስ ሰጥቶታል፡- «በራስህ ጽድቅ አትታመን፤ ላለፈው አትጨነቅ፤ ይልቁኑ አንደበትህንና ሆድህን ግዛ!»

7ኛ/ በአንድ ወቅት «ጠላት በዓለሙ ሁሉ ላይ ያጠመዳቸውን ወጥመዶች ተመለከትሁና ከእነዚህ ወጥመዶች ማን ሊያመልጥ ይችላል?» በማለት በሀዘን ውስጥ ሆኜ ስጠይቅ «ትሑት ሰው ያመልጣል» የሚል ድምፅ አደመጥሁ።» በማለት አባ እንጦንስ ተናግሯል።

8ኛ/ አባ እንጦንስ «አንዳንድ ሰዎች በምናኔ ሥጋቸውን መከራውን ቢያሳዩትም ቅሉ መረዳት በእነርሱ ዘንድ ስለሌለ እነርሱ ከእግዚአብሔር የራቁ ሰዎች ሆነው ይቀራሉ።» ብሏል።

9/ እንዲህም ብሎ ነበር፡- «በዚህች ምድር ላይ ስንኖር ሕይወታችንም ሆነ ሞታችን ከባልንጀራችን ጋር ነው። ወንድማችንን ገንዘብ ካደረግነው እግዚአብሔርን ገንዘብ እናደርገዋለን፤ወንድማችንን ካስቀየምነው ግን በክርስቶስ ላይ ኃጢአት እንሠራለን።»

10/ «ዓሣ ከውኃ ውስጥ ከወጣ በኋላ ለረኽቦም ጊዜ ከቆየ እንደሚሞት ሁሉ ከክአታቸው ውጮቱ የሚንቀዋለሉና ውድ ጊዜያቸውን ከኅለማው ያን ሰም ጋር የሚያላልፉ መነኩሳትም የውስጥ ሰላማቸውን ኃይል ያጡታል። ስለዚህ ዓሣ ወደ ባሕር ለመግባት እንደሚጣደፍ እኛም ወደ በአታችን ልንጣደፍ ይገባናል። ይህን የምናደርገውም በውጪ ከቆየን ውሳጣዊ ንቃታችንን እንዳናጣው በመፍራት ነው።» በማለት አባ እንጦንስ ተናግሯል።

11/ በአንድ ወቅት ደግሞ እንዲህ ብሏል፡- «በምድረ በዳ ብቻውን ለመኖር የሚመኝ ሰው ከሦስት ተቃዋሚ ነገሮች ነፃ ሊወጣ ይገባዋል። እነርሱም መስማት፣ መናገርና መመልከት ናቸው። ከእነዚህ ሌላ የሚቃረነው ተቃዋሚ ቢኖር ዝምታ ነው።

12/ ጥቂት ወንድሞች ወደ አባ እንጦንስ መጥተው የተመለከቱትን ራዕይ ሊነግሩትና ራዕዩ ትክክል መሆኑን አሊያም ርኩሳን መናፍስት ያሳዩአቸው መሆኑን ከእርሱ ለማወቅ ከነበሩበት ቦታ ተነሥተው ይመጣሉ። እነዚህ ሰምች ወደ አባ እንጦንስ በመምጣት ላይ እንዳሉ አንድ አህያቸው በመንገድ ላይ ሞቶ ነበር።

ሰዎቹ አባ እንጦንስ ያለበት ቦታ ሲደርሱ እነርሱ ጉዳያቸውን ከመናገራቸው በፊት «ያቺ ምስኪን አህያችሁ በመንገድ ላይ የመሞቷ ነገር ምንኛ አሳዛኝ ነው?!» በማለት ይነግራቸዋል።

እነርሱም «አባታችን . . . ይህን እንዴት ልታውቅ ቻልህ?» ብለው ሲጠይቁት . . .

«ምን እንደ ተፈጠረ ያሳዩኝ ርኩሳን መናፍስት ናቸው።» ይላቸዋል።

በዚህ ጊዜ «የመጣነው ይህንኑ ልንጠይቅህ ነበር። ማለትም በተደጋጋሚ እውነት ሆነው የሚቀየሩ ብዛት ያላቸው ራእዮችን ስለምንመለከት በዚህ መታሰላችንን ለመናገር ፈርተን ነበር።» አሉት።

በዚህ ዓይነት መንገድ ሽማግሌው አባ እንጦንስ የሞተችውን አህያ ምሳሌ በማድረግ ርዕያቸው የመጣው ከርኩሳን መናፍስት መሆኑን አሳምኖ መልሷቸዋል።

13/ አንድ አዳኝ አባ እንጦንስን በምድረ በዳ ውስጥ ከወንድሞቹ ጋር በደስታ ውስጥ ሆኖ ይመለከተውና ይደነግጣል። አንዳንድ ጊዜ የወንድሞችን ፍላጎት መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ለአዳኙ ሰው ሊያሳየው ስለ ፈለገ ሽማግሌው እንጦንስ «ቀስትህን ደጋኑ ውስጥ አስገባና አስፈንጥር!» አለው።

አዳኙም እንደ ታዘዘው አደረገ።

አባ እንጦንስ «ሌላም አስፈንጥር!» አለው።

አዳኙ አሁንም እንደ ተነገረው አደረገ።

ለሦስተኛ ጊዜ «አሁንም አስፈንጥር!» ሲለው፤

አዳኙ ሰው «የቀስቴን ደጋን ከዚህ የበለጠ ብለጥጠው ልሰብረው እችላለሁ።» በማለት ይመልስለታል።

በዚህ ጊዜ አባ እንጦንስ ለአዳኙ እንዲህ አለው፦

«የእግዚአብሔር አሠራርም እንዲሁ ነው። ወጣቶችን ልክ እንደ ደጋኑ ከመጠን አብዝተን በሥራ ልንወጥራቸው ከሞከርን ፈጥነው ይሰበራሉ። ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ ወጣቶች የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለመረዳት ከእነርሱ ጋር መዋል መልካም ነው።»

አዳኙ ሰው እነዚህን የአባ እንጦንስን ቃላት ሲሰማ በፀፀት ተሞላ። በመጨረሻም መንፈሱ ተነቃቅቶ ወደ መጣበት ሲመለስ በዚያ የነበሩት ወጣቶች ደግሞ ብርታት አግኝተው ወደየቤታቸው ሄዱ።

14/ በአንድ ወቅት ደግሞ አባ እንጦንስ አንድ በዕድሜ ገና ለጋ የሆነ መነኩሴ በመንገድ ላይ ተአምር በመሥራት ላይ መሆኑን ይሰማል። ይህ መነኩሴ ዕድሜያቸው ከመግፋቱ የተነሣ ለመራመድ እግሮቻቸውን ማንሣት ተቸግረው የነበሩ መነኮሳትን የዱር አህያዎች መጥተው ከተሸከሟቸው በኋላ አባ እንጦንስ እስካለበት ቦታ ድረስ እንዲያደርሷቸው ያዝዛል። የዱር አህዮቹ ተሸክመው ወደ አባ እንጦንስ ያደረሷቸው ሽማግሌዎች የሆነውን ሁሉ ለአባ እንጦንስ ይነግሩታል።

እርሱም «ይህ መነኩሴ ከወደቡ ዳር መድረሷን የማላውቅላትን አንዲት በሸቀጥ የተሞላች መርከብን መስሎ ይታየኛል።» አላቸው።

ይህን ተናግሯቸው ጥቂት እንደ ቆየ ድንገት ፀጉሩን እየነጨና እያለቀሰ የሐዘን እንጉርጉሮ ሊያወጣ ይጀምራል።

ይህን የተመለከቱ ደቀ መዛሙርቱ በመደናገጥ «አባታችን . . . ምን ሆነህ ነው የምታለቅሰው?» ብለው ይጠይቁታል።

እርሱም ለተማሪዎቹ «አንድ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ዓምድ አሁን ወድቋልና ሄዳችሁ የደረሰበትን ልታዩ ትችላላችሁ።» በማለት ወጣቱ መነኩሴ ያጋጠመውን እንዲመለከቱ ይልካቸዋል።

በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ ወደ መነኩሴው ፈጥነው ሲደርሱ በምንጣፍ ላይ ብቻውን ተቀምጦ ስለ ፈፀመው ኃጢአት ሲያለቅስ ያገኙታል።

መነኩሴው የአባ እንጦንስን ተማሪዎች ሲመለከት «እግዚአብሔር አሥር ቀናት እንዲሰጠኝ ይጸልይልኝ ዘንድ ጠይቁልኝ። እነዚህን ቀናት ካገኘሁ ደስተኛ እሆናለሁ።።» አላቸው።

ይሁን እንጂ ይህ መነኩሴ ከአምስት ቀናት በኋላ ሞተ።

15/ ወንድሞች መነኰሳት በአንድ ወቅት አንዱን መነኩሴ በአባ እንጦንስ ፊት ያመሰግኑታል። ይህ መነኩሴ አባ እንጦንስን ለማየት ወደ እርሱ ሲመጣ የሰዎችን ስድብ ምን ያህል መታገሥ እንደሚችል ይጠይቀዋል። መነኩሴው ፈጽሞ ሊታገሥ አለመቻሉን ከሁኔታው ሲረዳ «ውጪያዊ ገጽታው በጣም ያሸበረቀ ውስጡ ግን በወንበዴዎች የተዘረፈ መንደርን ትመስላለህ።» በማለት ተናገረው።

16/ አንድ ወንድም በአንድ ወቅት አባ እንጦንስን «ጸልይልኝ» በማለት ይጠይቀዋል።

እንጦንስም «አንተ ራስህ ጥረት የማታደርግና ወደ እግዚአብሔር የማትጸልይ ከሆነ እኔም ሆንሁ እግዚአብሔር ምሕረት ልናደርግልህ አንችልም!» አለው።

17/ አንድ ጊዜ ደግሞ ጥቂት በዕድሜ የገፉ ሰዎች ከአባ እንጦንስ ጋር ለመገናኘት ወደ እርሱ ይመጣሉ። ከእነርሱ ጋር አባ ዮሴፍም ነበር። እነዚህን ሰዎች መፈተን የወደደው አባ እንጦንስ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ጠቅሶ ቃላቱ ምን ለማለት እንደ

ተነገሩ በሰድማ ዝቅተኛ ከሆነው አንስቶ እስከ ታላቁ ድረስ በቅደም ተከተል ይጠይቃቸዋል። ሁሉም የሚያውቁትንና የተረዱትን ይመልሱለታል።

እርሱም ሁሉም ትክክል ስላልመለሱለት «የጠየቅኋችሁን አልተረዳችሁትም!» ይላቸዋል።

በመጨረሻም ወደ አባ ዮሴፍ መለስ ብሎ «አንተስ ይህንን አባባል እንዴት ልታብራራልኝ ትችላለህ?» በማለት ይጠይቀዋል።

አባ ዮሴፍ ግን «እኔ አላውቅም!» በማለት ይመልስለታል።

በዚህ ጊዜ አባ እንጦንስ ሌሎቹን እየተመለከተ «አባ ዮሴፍ አላውቅም ብሎ በመመለሱ እርሱ ትክክለኛውን መንገድ አግኝቶታል።» አላቸው።

18/ አንድ ጊዜ ጥቂት ወንድሞች አባ እንጦንስን ለማግኘት ሴቲስ (Scetic) ከምትባል ቦታ ተነሥተው ይሄዳሉ። ወደ እርሱ በመጓዝ ላይ እንዳሉ ባሕሩን መሻገር ስለ ነበረባቸው ታንኳ ላይ ይሳፈራሉ። ታንኳዋ ላይ ሲሳፈሩ እነርሱ ወደሚሄዱበት ቦታ የሚሄድ አንድ ሽምገል ያለ ሰው አገኙ። እነዚህ ወንድሞች የዚህን ሰው ማንነት አላወቁም።

ብቻ በገዛአቸው ላይ ሳሉ ስለ አባቶች ቃል፣ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍትና ስለ ግል ሥራዎቻቸው በየተራ ሲወያዩ ሽማግሌው

ሰው ዝም ብሎ ያደምጣቸው ነበር። ሁሉም ወደ ወደቡ ከደረሱ በኋላ ሽማግሌውም ሰው እነርሱ ወደሚሄዱበት ወደ አባ እንጦንስ በእት የሚሄድ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

እዚያ እንደ ደረሱም አባ እንጦንስ፦ «ብዛአችሁ ላይ ይህን ሽማግሌ መልካም ሰው ሆኖ አገኛችሁት?» በማለት ይጠይቃቸዋል።

በዚያ ያገኙትም ሰው በጉዞ ላይ ለነበረው ሽማግሌ «አባቴ ሆይ! ብዙ ባይባሉም ጥቂት መልካም ወንድሞችን ይዘህ መጥተሃል!» አለው።

በዚህ ጊዜ አባ እንጦንስም «በእርግጥም መልካም ወንድሞች ናቸው። ይሁኑ እንጂ ለቤታቸው መዝጊያ ስለሌለው መግባት የፈለገ ሁሉ ወደ ጋጣው በመግባት አህያውን ፈትቶ መውሰድ ይችላል።» አለው።

እዚህ ላይ አባ እንጦንስ ስለ እነዚህ ወንድሞች ሲናገር የወደደው «የሚያወሩት ወደ አፋቸው የመጣውን ሁሉ ነው!» ለማለት ነው።

19/ በአንድ ወቅት ደግሞ ጥቂት ወጣቶች ወደ አባ እንጦስ ተሰብስበው በመሄድ «እንዴት እንደምንድን አንድ ነገር ንገረን!» አሉት።

እርሱም «መጻሕፍትን ካነበባችሁ እነርሱ... እንዲት እንደምትድኑ ይነግሯችኋል፤ ያድኗችኋልም።» ይላቸዋል።

ወጣቱቹም «አባታችን! እኛ የምንፈልገው አንተ እንድትነግረን ነው!» አሉት።

በዚህ ጊዜ ሽማግሌው አባ እንጦንስ እንዲሁ እንደማይለቱት ስላወቀ «ወንዴል . . . 'ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለማመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ስጠው' ይላል።» (ማቴ 5:39) ይላቸዋል።

እነርሱም «ይህንንማ ልናደርገው አንችልም!» ይሉታል።

አባ እንጦንስም መልሶ «ሌላኛውን ጉንጫችሁን ማዞር ባትችሉም እንኳ አንዱ መመታቱን ፍቀዱ!» ይላቸዋል።

«ይህንንም ልናደርገው አይቻለንም!» በማለት ይመልሱለታል።

በዚህ ጊዜ ቀጠል አድርጎ «ይህንንም ማድረግ ካልቻላችሁም ከፊሉን በከፊሉ ለመመለስ አትሞክሩ!» አላቸው።

እነርሱ ግን ይህንንም ማድረግ እንደማይሆንላቸው ይነግሩታል።

በዚህ ጊዜ አባ እንጦንስ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መለስ ይልና «ለእነዚህ ወጣቶች ጥቂት የበቆሎ ጠላ አዘጋጁላቸው። ይህንንም ያንንም ማድረግ ካልቻላችሁ ሌላ ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ? እናንተን የሚያስፈልጋችሁ ጸሎት ብቻ ነው» ይላቸዋል።

20/ አንድ ወንድም ዓለምን በመናቅ ያለውን ሁሉ ሸጦ ለድሆች ካከፋፈለ በኋላ ለግል ፍጆታው አንድ ተሰጥኦው ጥቂት ገንዘብ ያስቀራል። ከዚህ በኋላ አባ እንጦንስን ለማየት ወደ እርሱ ይሄድና ያደረገውን ሁሉ ይነግረዋል።

አባ እንጦንስም «መንኩሴ ለመሆን ከፈለግህ ወደ መንደር ተመልሰህ ሂድና ሥጋ ከገዛህ በኋላ በዚያ ሥጋ ዕርቃንህን ሸፍነውና ወደዚህ ተመልሰህ ና!» ይለዋል።

ሰውየውም የተነገረውን አድርጎ ወደ አባ እንጦንስ ሲመለስ ውሾችና አሞራዎች ሰውነቱን ይዘነጣጥሉታል። ወደ ሸማግሌው መነኩሴ ተመልሶ ሲመጣ የታዘዘውን በትክክል መፈጸምና አለመፈጸሙን ይጠይቀዋል።

በዚህ ጊዜ ሰውየው የተነካከሰ ገላውን ገልጦ ሲያሳየው አባ እንጦንስ «ዓለምን ንቀናል ካሉ በኋላ ለራሳቸው ፍጆታ የሚሆን ነገር የሚያስቀሩ ሰዎችም ልክ እንደዚሁ በእነርሱ ላይ ውጊያ በሚከፍቱ ርኩሳን መናፍስት አማካይነት ይዘነጣጠላሉ!» በማለት አስተምሮታል።

21/ በአንድ ወቅት አንድ ወንድም በአባ ኤልያስ ገዳም ውስጥ እንዳለ ይፈተናል። በዚህ ጊዜ ይህ ሰው ከገዳሙ ይወጣና አባ እንጦንስ ወዳለበት ተራራማ ሥፍራ ይሄዳል። በዚያ ጥቂት ከቆየ በኋላ አባ እንጦንስ ወደ ተባረረበት ገዳም መልሶ ይልከዋል።

በዚያ ያሉት መነኮሳት ወንድሞች መልሰው ሲያባርሩት ተመልሶ አባ እንጦንስ ወዳለበት ይሄድና «አባቴ ሆይ! መነኮሳት ወንድሞቼ ሊቀበሉኝ አልፈቀዱም!» ይሰዋል።

በዚህ ጊዜ አባ እንጦንስ እንዲህ የሚል መልዕክት በዚህ ሰው ይልክባቸዋል፦ «አንዲት ታንኳ በባሕር መካከል እንዳለች አደጋ ይደርስባትና የጫነችው ንብረቷን ታጣለች። ይሁን እንጂ እንደ ምንም ብላ ወደ ወደቡ ትደርሳለች። እናንተ ግን ወደ ወደቡ በሰላም የደረሰችውን ታንኳ መልሳችሁ ወደ ባሕሩ መካከል ልትወረውሯት እየታገላችኋት ነው።»

በዚያ ገዳም ውስጥ የነበሩት መነኮሳት ይህን አባ እንጦንስ የላከውን መልዕክት ስለ ተረዱ መነኮሱን መልሰው ሊቀበሉት ቻሉ።

22/ በአንድ ወቅት አባ እንጦንስ፦ «ሥጋ ተግባሩ አድርጎ የለመደው የተፈጥሮ እንቅስቃሴ እንዳለው አምናለሁ። ይሁን እንጂ ከነፍስ ፈቃድ ውጪ ይህን ሊከተል አይችልም። እንዲህ ያለው ነገር የሚያሳየው ሰውነት ያለ ስሜት መንቀሳቀሱን ነው።

ሌላም ዓይነት እንቅስቃሴ አለ። ይህ እንቅስቃሴ ሰውነትን ከመመገብና ከማሟሟቅ ወይም ከበሉና ከጠጡ በኋላ የሚመጣ እንቅስቃሴ ነው። ይህ ደግሞ ደምን ስለሚያሞቅ ሰውነትን ስለሚበጠብጠው ሥራን በትክክል እንዳይሠራ ያደርገዋል። ሐዋርያው «ብወይን ጠጅ አትስከሩ!» (ኤፌ 5፡18) ያለው በዚህ ምክንያት ነው።

በወንጌልም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ተናግሮናል፦ «ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በሰካር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ . . . ሰራሳችሁ ተጠንቀቁ።» ሉቃ 21:34።

ከዚህም በተጨማሪ ሌላ ዓይነት እንቅስቃሴ አለ። ይህ እንቅስቃሴ ከሚዋጉ ሰዎች ዘንድ የሚመጣ ሲሆን ይህ ደግሞ ምንጩን ያደረገው ከርኩሳን መናፍስት ማታለያና ቅንዓት ነው።

እነዚህን ሦስት ዓይነት የሰው እንቅስቃሴዎች ልትረዷቸው ይገባል። የመጀመሪያው እንቅስቃሴ የተፈጥሮ እንቅስቃሴ ሲሆን፣ ሁለተኛው እንቅስቃሴ ብዙ ከመብላትና ከመጠጣት የሚመጣ ነው። ሦስተኛውና የመጨረሻው እንቅስቃሴ ደግሞ ከርኩሳን መናፍስት የሚመጣ እንቅስቃሴ ነው።» በማለት ተናግሯል።

23/ «አስቀድሞ የደረሱ ተመሳሳይ ውጊያዎች በዚህ ትውልድ ላይ ይደርሱ ዘንድ እግዚአብሔር አይፈቅድም። ምክንያቱም አሁን ያሉት ሰዎች ደካሞች ስለሆኑና ፈጽሞ

ሊቋቋሟቸው ስለማይችሉ ነው።» በማለት አባ እንጦንስ ተናግሯል።

24/ አባ እንጦንስ በምድረ በዳ ሳለ በከተማ ውስጥ ከእርሱ ጋር በብቃት እኩል የሆነ ሰው እንዳለ ተገልጦ ይታየዋል። ይህ ሰው በመያው ሐኪም ሲሆን ለእርሱ ከምትበቃው ጥቂት ነገር ውጪ የሚያገኘውን ሀሉ ለድሆች ይሰጣል። ታዲያ ይህ ሰው በየዕለቱ ከቅዱሳን መላእክት ጋር አብሮ ይዘምር ነበር።

አባ አርሳኔምስ

(ABBA ARSENIUS)

አባ አርሳኔምስ የተወለደው በ360 ዓ.ም. ሮም ውስጥ ነው። ይህ ጠለቅ ያለ እውቀትና ከፍ ያለ ማዕረግ ያለው ሰው በንጉሡ በቀዳማዊ ቴዎዶስዮስ ትዕዛዝ ልዑላኑ አርቃዴምስንና ሆኖሬምስን እንዲያስጠና ከፍተኛ ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር። ይሁን እንጂ በ394 ዓ.ም. በምሥጢር ከቤተ መንግሥቱ በመውጣት በመርከብ ተሳፍሮ ወደ እስክንድርያ ይሄዳል። ከዚህ በኋላ ሴቲስ ወደምትባለው ቦታ በመግባት ራሱን በአጭሩ በአባ ዮሐንስ መሪነት ሥር ያገኘዋል። ከዚያም መቀመጫውን ሴቲስ ውስጥ በምትገኘው ፒትራ በምትባል መንደር ውስጥ ያደርጋል። በእርሱ ሥር የነበሩት ሦስት ደቀ መዛሙርት ሲሆኑ እነርሱም እስክንድር፣ ዞይለስና ጳንኤል ይባሉ ነበር። አባ አርሳኔምስ የሚታወቀው ከማንም በበለጠ በትህትናውና በአርምሞው ሲሆን ይህም ከነበረው ታላቅ እውቀት ጋር መዋሐዱ በግብጽ መነኩሳት ዘንድ ልዩ ሰው አድርጎት ነበር። በ434 ዓ.ም. ከደረሰው ከሁለተኛው የሴቲስ ጥፋት በኋላ ከዚያ ወጥቶ ትሮይ (Troe) ወደሚባለው ተራራ ሄዶ በ449 ዓ.ም. በሞት እኪያርፍ ድረስ ቀሪውን የሕይወቱን ጊዜ በዚያ አሳልፏል።

፲ኛ/ አባ አርሳኔምስ በቤተ መንግሥት ሳለ ከዕለታት አንድ ቀን «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! እባክህ የድኀነትን መንገድ አሳየኝ!» ብሎ ሲጸልይ «ከሰዎች ርቀህ ከሄድህ ድኀነትን ታገኛለህ!» የሚል ድምፅ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጣለት።

2ኛ/ አባ አርሳኔምስ ይህን ቃል ሰምቶ ወዲ ብሕትውና ሕይወት ውስጥ ከገባ በኋላ ለሠላሳኛ ጊዜ ይህንኑ ጸሎት ደግሞ ይጸልያል።

በዚህ ጊዜ አስቀድሞ ወደ አርሱ የመጣው ድምፅ፡ «አርሳኔምስ . . . ሽሽ! ዝም በል! ሁልጊዜ ጸልይ! . . . ከኃጢአት ነጻ ለመሆን ብቸኛዎቹ መንገዶች እነዚህ ናቸውና!» አለው።

3ኛ/ አባ አርሳኔምስ በበአቱ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ርኩሳን መናፍስት ከፉኛ ሊነዘንዙት ይጀምራሉ።

በዚህ ጊዜ ከበአቱ ውጪ በደጃፉ ላይ ቆመው የነበሩት ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ እያለ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ ይሰሙታል፡

«ጌታዬ ሆይ! በፊትህ ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ባልሠራም እንደ ቸርነትህ አቁመኸኛል! ስለዚህ ከአሁን በኋላ መልካም መሥራትን ስለምጀምር እባክህ አትተወኝ!»

፭ኛ/ ስሉ አባ አርሳኔምስ እንዲህ ተብሏል፡

«አርሰ· በቤተ መንግሥት ውስጥ ሳለ የለበሳቸውን ድንቅ ድንቅ አልባሳት ማንም አልለበሰም። አሁን ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር እያለ አርሰ· የለበሳቸውን ያረጁና የተበጣጠሰ· ልብሶች የለበሰ ማንም የለም።»

5ኛ/ አንድ ሰው የተቀደሰው አባ አርሳኔምስ፦ «እኛ ባለን ከፍተኛ ትምህርትና የጠለቀ እውቀት የትም ልንደርስ አልቻልንም! እነዚህ የግብፅ ባላገሮች ግን የበዛ አስደናቂ መልካምነት· አላቸው። ይህ እንዴት· ሊሆን ቻለ?» በማለት ጠየቀው።

አርሰ·ም እንዲህ ሲል መልሶለታል፦ «በእርግጥ እኛ ከዓለማዊው· እውቀታችን ያገኘነው ነገር የለም! እነዚህ የግብፅ ገበሬዎች (መነኩሳት) ግን በብዙ· ድካምና ህመም መልካምነታቸውን ሊያገኙ· ችለዋል።»

6/ ከዕለታት አንድ ቀን አባ አርሳኔምስ ስለሚያስበው· ነገር ለአንድ ተራ· ግብፃዊ ገበሬ ያማክረዋል።

ይህን ሲያደርግ የተመለከተው· አንድ ሰው ወደ አርሰ· ጠጋ ብሎ «አባ አርሳኔምስ ሆይ! አንተ ታላላቅ የተባሉት የላቲንና የግሪክ እውቀት አያለህ ስለ አሳብህ እንዴት ይህንን ገበሬ ትጠይቃለህ?» በማለት ጠየቀው።

አርሳኔምስም «በእርግጥ የላቲንና የግሪክ ሙሉ እውቀት አለኝ። ይሁን እንጂ የዚህን ሰው ፊደል አላውቀውም!» ብሎ መልሶለታል።

7/ ከዕለታት አንድ ቀን ሊቀ ጳጳሱ ቴምፍሎስን (Theophilus) ካህናቱ በክብር እንደ አጀቡት ወደ አባ አርሳኔምስ ይሄዳል። ከዚያም ከቃሉ በረከት ለመቀበል ጠጋ ብሎ ይጠይቀዋል።

ዕድሜው በመግፋት ላይ ያለው አባ አርሳኔምስ ከጥቂት ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ ወደ እርሱ የመጡትን አንድ በአንድ ተመለከታቸውና «እኔ የምነግራችሁን ሁሉ ተግባር ላይ ታውሉታላችሁን?» በማለት ይጠይቃቸዋል።

ሁሉም ሊቀ ጳጳሱን ተከትለው በአንድ ድምፅ እንደሚያውሉት ቃል ገቡለት።

አባም «አርሳኔምስ በዚህ ቦታ ይገኛል የሚል ነገር ከሰማችሁ ወደዚያ አትሂዱ!» አላቸው።

8/ በሌላ ጊዜ ሊቀ ጳጳሱ እርሱን ማየት ስለ ወደደ ከመልዕክተኞቹ አንዱን ወደ እርሱ ልኮ ቢመጣ ሊቀበለው መቻል አለመቻሉን እንዲጠይቀው ያደርጋል።

አባ አርሳኔምስ «ከመጣህ ልቀበልህ እችላለሁ። አንተን ከተቀበልህ ደግሞ ሁሉንም ሰው መቀበል አለብኝ። ይህን የማደርግ ከሆንህ ደግሞ እዚህ መኖር አልችልም!» በማለት መልሶ ይልክበታል።

ሊቀ ጳጳሱም የተላከበትን መልዕክት ከመልዕክተኛው ሲሰማ «እኔ ወደ እርሱ በመሄዴ አሁን ካለበት ቦታ እንዲሰደድ የማደርገው ከሆነ ከአሁን በኋላ አልሄድም!» ብሎ አሳቡን እስከ መጨረሻው ሰርዟል።

9/ በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ ወጣት ከቃሉ በረከት ሊቀበል ወድዶ ወደ አባ አርሳኔምስ መጣና ጥያቄ ጠየቀው።

አርሳኔምስም «ባለህ ኃይል ሁሉ በውስጥህ ያለው እንቅስቃሴ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር አንድ እንዲሆን ታላቅ ጥረት አድርግ። ይህን ካደረግህ በውጪ ያለ ፍላጎትህን ማሸነፍ ትችላለህ!» በማለት ታላቅ መንፈሳዊ ምክር ለገሠው።

10/ በአንድ ወቅት አባ አርሳኔምስ «እግዚአብሔርን ከፈለግነው ራሱን ይገልጥልናል! ከእኛ ጋር እንዲሆን ካደረግነው ደግሞ ከእኛ አይለይም!» ብሎ ተናግሯል።

11/ አንድ ቀን አንድ መነኩሴ ወደ አባ አርሳኔምስ ቀርቦ «ሕሊናዬ እንዲህ እያለ እያወከኝ ነው፡- ልትጸምም ሆነ ልትሠራ አትችልም! ስለዚህ የታመመውን መጎብኘትም መልካም ሥራ

ስለሆነ በሽተኞቹን አለበት ቦታ ድረስ ሂድና ጠይቃቸው እያለኝ ነው!» ብሎ ይነግረዋል።

አባ አርሳንዮስም ይህ የርኩስ መንፈስ ክፉ ምክር መሆኑን ስለ ተገነዘበ ለመነኩሴው፡- «ተነሥተህ ሂድና - ብላ፣ ጠጣ፣ ተኛ፣ ሥራም አትሥራ! ነገር ግን ከበአትህ አትውጣ!» አለው።

አባ አርሳኔዎስ ይህን የተናገረው በበአት ውስጥ መጽናት አንድ መነኩሴን በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዝ ያደርገዋል የሚል እምነት ስለ ነበረው ነው።

12/ አባ አርሳኔዎስ «ርቆ ወደ ውጪ የሚጓዝ መነኩሴ በምንም ነገሮች ውስጥ ራሱን ማጠላለፍ የለበትም። ይህን ካደረገ በሰላም ይቆያል!» በማለት አብዝቶ ይናገር ነበር።

13/ አባ ማርቆስ በአንድ ወቅት አባ አርሳኔዎስን «ለምንድር ነው የምታገልለን?» በማለት ጠየቀው።

«አንደምወዳችሁ እግዚአብሔር ያውቃል። ይሁን እንጂ በአንድ ጊዜ ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር መኖር አልችልም፤ አልፍ አልላፉት የሆኑት መንፈላውያን የሰማይ ሠራዊት ያላቸው ፈቃድ አንድ ነው። የሰዎች ፈቃድ ደግሞ ብዙ ናቸው። ስለዚህ ከሰዎች ጋር ለመሆን ብዬ እግዚአብሔርን አልተውም!» በማለት መልሷል።

14/ አባ አርሳኔዎስ ሌሊቱን ሙሉ ሳይተኛ ካደረ በኋላ የተፈጥሮ ግዴታ ስለሆነ ሊነጋጋ ሲል እንቅልፍ አናውዞ እንዲተኛ ሲያስገድደው «አንተ ክፉ አገልጋይ! . . . እስቲ ና!» በማለት እንቅልፍን ይናገረው እንደ ነበር ደቀ መዝሙሩ አባ ዳንኤል ተናግሯል። ከዚህ በኋላ በተቀመጠበት ቦታ ላይ ጥቂት ያንቀላፋና ወዲያውኑ ነቅቶ ተግባሩን ማከናወን ይጀምራል።

15/ «ለመልካም ተዋጊ መነኩሴ የአንድ ሰዓት እንቅልፍ በቂው ነው!» እያለ አባ አርሳኔዎስ ይናገር ነበር።

16/ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው በሴቲስ ውስጥ ጥቂት የደረቁ የበለስ ፍሬዎች እንደሚያድል አንድ ሽማግሌ ሰው ይናገር ነበር። እነዚህ የበለስ ፍሬዎች ደርቀው ስለ ነበርና ብዙ ጥቅም ስላልነበራቸው ሁሉም የአባ አርሳኔዎስ ስሜት ላለመገዳት ወደ እርሱ ሊወስዱለት አልፈቀዱም። ይህን የሰማው አርሳኔዎስ ይህ ገዳይ ወደ ተፈጸመበት ቦታ ለመሄድ ሳይወድ ቀረ።

ለሰዎቹም «እግዚአብሔር ለወንድሞቼ ያደላቸውንና እኔ ልቀበለው የማይገባኝን በረከት እንዳልካፈል ከመካከላችሁ ለይታችሁኛል።» አላቸው።

ሁሉም ይህን ሲሰሙ በአረጋዊው በአባ አርሳኔዎስ ትሕትና ተነቃቁ። ከዚህ በኋላ አንደኛው ካህን ጥቂት የደረቁ የበለስ ፍሬዎች ይዞለት ከሄደ በኋላ በደስታ ወደ ወንድሞቹ ይዞት ሊመጣ ችሏል።

17/ አባ ዳንኤል ስለ አባ አርሳኔዎስ አመጋገብ እንዲህ ይል ነበር፦

«እርሱ ከእኛ ጋር ለረኻቦም ዘመናት ሲኖር በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ አንድ ቅርጫት መሉ ዳቦ እንወስድለት ነበር። ዓመቱን ጠብቀን ሌላ አንድ ቅርጫት ዳቦ ይዘንለት ስንሄድ አምና ከወሰድንለት ዳቦ እንድንበላ ያቀርብልን ነበር።»

18/ አባ አርሳኔዎስ የመጠጥ ፍጆታው ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ነበረው። ከዘምባባው ቅጠሎች ላይ ተንጠባጥቦ የሚጠራቀምለትን ውኃ የሚቀይረው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። በሌላው የዓመቱ ጊዜ የሚያደርገው ውኃውን በማጠራቀሚያው ላይ ከላይ ከላይ መጨመር ብቻ ነው።

ይህን የተመለከተ አንድ አረጋዊ አባት «ሽቱና መልካም መዓዛ ያለው ይመስል የዚህን የዘምባባ ቅጠል የቆየና ሽታው የከረፋ ውኃ ማቆየትህ ስለ ምንድር ነው?» ብለው ሲጠይቁት፣

አባ አርሳኔዎስ እንዲህ በማለት መልሰላቸዋል፦ «በዚህ ዓለም ስኖር እንዲህ ያለውን መጥፎ ሽታ ልቋቋም ይገባኛል!»

19/ የተለያዩ ፍራፍሬዎች ጊዜያቸው ደርሶ ሲበስሉ አባ አርሳኔዎስ ደቀ መዛሙርቱን «ጥቂት ቀጥፋችሁ አምጡልኝ!» ብሎ ይልካቸዋል። ከዚያም ከእያንዳንዱ ፍሬ በጣም በትንንሽ ከቀመሰ በኋላ የምድር ፍሬ ጌታ የሆነውን እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

20/ በአንድ ወቅት አባ አርሳኔዎስ ሲታመም በሰውነቱ ላይ የቀረው ጥቂት ዕራፊ ጨርቅ ብቻ ነበረ። በወቅቱ ጨርቅ የሚገዛበት ምንም ነገር ስላልነበረው ከሌላ ቦታ በምጽዋት ሊቀበል ግድ ሆኖ ነበር።

አባ አርሳኔዎስ በምጽዋት ያገኘውን ጨርቅ ከተቀበለ በኋላ «እቤቱ ጌታዬ ሆይ! በስምህ ይህን ምጽዋት እንድቀበል ስላደረግኸኝ አመሰግንሃለሁ!» በማለት ፈጣሪውን አመስግኗል።

21/ ምንም እንኳ በአቱ ከሱቲስ አምሳ አንድ ኪ.ሜ. ብትርቅም ሰዎች ይላላኩት ስለ ነበር ለቋት ሊሄድ ፈቃደኛ አልነበረም።

ሱቲስ በወደመች ጊዜ እያለቀሰ ሲወጣ «ዓለም ሮምን ስትጣ መነነሳት ግን ሱቲስን አጥተዋል!» በማለት ተናግሯል።

22/ በአንድ ወቅት አባ ማርቆስ «በበአትህ ውስጥ ትርፍ የሆነ ነገር ማስቀመጥ መልካም ነውን? አንድ የተለያዩ የምግብ አትክልት የነበሩት ወንድሜ በሙሉ ነትሎ ሲጥል ተመልክቼያለሁ።» በማለት አባ አርሳኔዎስ ይጠይቀዋል።

እርሱም «በእርግጥ ይህ መልካም ነው። ሊወሰድ የሚገባው የብቃት እርምጃ ግን እንደ ሰውየው ብቃት ሊወሰን ይገባል። ይህ ሰው ይህንን ለማድረግ ልምዱና ብቃቱ ከሌለው ጥቂት ቆይቶ ሌላ አትክልት መትከሉ እርግጥ ነው።» በማለት መልሶለታል።

23/ የአባ አርሳኔዎስ ደቀ መዝሙር የነበረው አባ ጳንኤል በአንድ ወቅት እንዲህ በማለት ነገሮችን አነሳሥሯል፡-

«ከዕለታት አንድ ቀን እኔነቴን ከአባ እስክንድር አጠገብ ባገኘውም እርሱ ግን በጎዘን ውስጥ ነበር። ያገኘሁት ጊዜ በጎዘኑ ምክንያት በጀርባው ተጋድሞና ዐይኖቹን ወደ ላይ አፍጥጠ ይመለከት ነበር። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ቅዱስ አባ አርሳኔዎስ ከእርሱ ጋር ለመነጋገር ወደ እርሱ ይመጣል።

በንግግራቸውም መካከል አባ አርሳኔዎስ «ቅድም እዚህ ጋ ተጋድሞ የተመለከትኩት ሰው ማነው?» በማለት ይጠይቃል።

አባ እስክንድርም «እዚህ ዘንድ ነው የተመለከትኸው?» ብሎ መልሶ ይጠይቀዋል።

አባ አርሳኔዎስ «ከተራራው ጫፍ ወደዚህ ስወርድ ዓይኖቼን ወደዚህ በአት ወርውሬ ነበር። በዚያን ጊዜ አንድ ሰው በጀርባው ተዘርግቶ በመጋደም ወደ ሰማይ አፍጥጦ ሲመለከት አይቼያለሁ።» አለው።

በዚህ ጊዜ አባ እስክንድር ንስሓ እየገባ «አባቴ ሆይ! እኔ ስለ ነበርሁ ይቅር በለኝ! በጎዘን አዘቅት ውስጥ ስለ ወደቅሁ ነው!» ብሎ ይነግረዋል።

በዚህ ጊዜ አባ አርሳኔዎስ «ይሁን! ለካስ አንተ ነብርህ? እኔ እኮ የጠየቅሁህ አንድ መንገደኛ ሰው ስለ መሰልኸኝ ነው!» አለው።

24/ በሌላ ጊዜ ደግሞ አባ አርሳኔዎስ ለአባ እስክንድር «የዘምባባ ቅጠሉችህን ቆርጠህ ስታበቃ ወደ እኔ መጥተህ ምግብህን ከእኔ ጋር አብረህ ብላ። እንግዶች ከመጡብህ ግን ከእነርሱ ጋር ብላ።» ይለዋል።

አባ እስክንድርም ሥራውን በዝግታና በጥንቃቄ መሥራቱን ይቀጥላል። ሰዓቱ ሲደርስ የታዘዘለውን ሥራ ስላላጠናቀቀ እስኪጨርስ ድረስ የአባቱን ትዕዛዝ ለመፈፀም ሲል በዚያው ይቆያል። በዚህ ጊዜ አባ አርሳኔዎስ ተማሪው ሲዘገይበት እንግዶች መጥተውበት ይሆናል ብሎ በማሰብ ምግቡን ይበላል። በመጨረሻ ግን አባ እስክንድር ሥራውን ፈጽሞ ወደ እርሱ ይሄዳል።

አባ አርሳኔዎስ «እንግዶች መጡብህ እንዴ?» በማለት ይጠይቀዋል።

እርሱም «አልመጡብኝም!» ብሎ መለሰለት።

«ታዲያ ለምን አልመጣህም?» ብሎ ይጠይቀዋል።

«ወደ አንተ እንድመጣ የፈቀድህልኝ ቅጠሎቹን ቆርጬ ላበቃ ነው። ስለሆነም ቆርጬ የጨረስሁት ገና አሁን ስለሆነ

ትእዛዝህን ለመጠበቅ ስል ሳልጨርስ ወደ አንተ ልመጣ ስላልፈቀድሁ ነው።» ብሎ ይመልስለታል።

በዚህ ጊዜ አረጋዊው መነኩሴ አባ አርሳንዮስ በተማረው ቃል ጠባቂነት በመደነቅ «የጸሎት ጊዜህን ያለ ምንም ችግር ማከበር እንድትችል ጥቂት ውኃ ጠጣ! አለበለዚያ ሰውነትህ ሊጎዳብህ ይችላል።» ብሎ መከረው።

አባ ዳንኤል

(ABBA DANIEL)

አባ ዳንኤል የአባ አርሳኔምስ ደቀ መዝሙር ነበር። በ449 ዓ.ም. አባ አርሳኔምስ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በአጠገቡ ተገኝቷል። በዚያን ጊዜ የቅዱስ አባ አርሳኔምስ ተማሪ የነበረውና ቀሚሱን፣ ጠጉሩን፣ ካናቴራውንና የጠጉር ሚማውን የተረከበው አባ ዳንኤል «ልለብሳቸው የሚገባኝ ሰው ባልሆንም በረከቱን ግን እቀበልበታለሁ!» በማለት ተናግሮ ነበር።

1/ አረመኔዎች ሴቲስን በወረሩ ጊዜ በዚያ የነበሩ መነኮሳት አባቶች ከዚያ ሸሽተው ሲሄዱ የተመለከተው አባ ዳንኤል «እግዚአብሔር የማይጠብቀኝ ከሆነ እስከ ዛሬ ድረስ ለምን ኖርሁ?» በማለት ተናግሮ ካበቃ በኋላ አረመኔዎቹ ሳያዩት በመካከላቸው አድርጦ ሄዷል።

ከዚህ በኋላ ለራሱ «ተመልከት! እግዚአብሔር ስለ ጠበቀኝ አልሞትሁም! ካሁን በኋላ ግን እንደ ሰው ሰውኛው አካሄድ ከአባቶቼና ከወንድሞቼ ጋር አብሬ እሸሻለሁ!» በማለት ተናግሯል።

2/ አንድ ላመጣት መነኮስ ወደ አባ ዳንኤል ቀርቦ «አባቴ ሆይ! አንድ ትዕዛዝ ስጠኝና ልጠብቀው!» ብሎ ጠየቀው።

«እጅህን ከሴት እጅ ጋር ወደ ወጭቱ ውስጥ አታስገባ፤ ከእርሷ ጋር አትብላ፤ይህን ከጠበቅህ የዝሙትን መንፈስ ልትርቀው ተችላለህ!» በማለት መልሶለታል።

3/ አንድ ጊዜ አባ ዳንኤል እንዲህ ብሎ ሲናገር ተደምጧል፦ «ባቢሎን ውስጥ የአንድ የታወቀ ሰው ሴት ልጅ በርክሳን መናፍስት ትያዛለች። አባቷ አጥብቆ የሚወደው አንድ መነኩሴ ወደ እርሱ ቀርቦ 'እኔ ከማውቃቸው የበረሃ አባቶች በስተቀር ልጅህን ማንም ሊያድናት አይችልም! ይሁን እንጂ እነዚህን አባቶች ልጅህን እንዲያድኑልህ ብትጠይቃቸው ከትሕትናቸው ብዛት እሺ አይሉህም! ስለዚህ እኔና አንተ እንዲህ እናድርጋለን . . . እነርሱ ወደ ገበያ ሲመጡ አንተ ያመጡአቸውን ዕቃዎች የምትገዛ መስለህ ቅረባቸው፤ከዚያም የዋጋ ድርሻቸውን ሊቀበሉህ ሲቀርቡ ጸሎት እንዲያደርጉልን እንጠይቃቸዋለን። በዚህ ጊዜ ልጅህ ትድናለች!' በማለት ያማክረዋል።

በዚህ ተስማምተው ወደ ገበያ ሲመጡ የእነዚያ አባቶች ተማሪ የሆነ አንድ ሰው በመንገድ ዳር ተቀምጦ ዕቃዎቻቸውን ሲሸጥ ያገኙታል። ከዚያም ተማሪያቸው ስለሆነው ለዚህ መነኩሴ ትርጫቱን አሸክመው ዋጋውን ይቀበል ዘንድ እየመሩ ልጅቷ ወዳለችበት ቤት ይዘውት ይሄዳሉ። ወደ ቤት እንደ ደረሱ በርክሳን መናፍስት የተያዘችው የሰውየው ሴት ልጅ ከቤት ውስጥ ወጥታ ሐሳቡን ሊቀበል የመጣውን መነኩሴ ከፋኝ በጥፊ ትመታዋለች። በዚህ ጊዜ መነኩሴው እንደ ጌታ ትእዛዝ ሁለተኛ ጉንጩን ያሰራል። (ማቴ 5:39።)

ዲያብሎስን ይህ ትሕትና እንደ አሳት ስላቃጠለው በከፍተኛ ድምፅ እየጮኸ «እንዴት ያለ ኃይል ነው?! የኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ ከዚህ አስወጣኝ!» አለ። በዚህ ቅጽበት ውስጥ ልጅቷ ተፈወሰች።

እነዚያ አባቶች ሲመጡ የሆነውን ነገር ሁሉ ሲያጫውቷቸው፤ «የዲያብሎስ ትዕቢት የሚዋረደው በዚህ በክርስቶስ የትሕትና ትእዛዝ ብቻ ነው!» እያሉ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና አቀረቡ።

4/ በሌላ ጊዜ አባ ዳንኤል፦ «ሥጋ የሚበረታው ነፍስ በደከመችበት መስፈሪያ መጠን ሲሆን ነፍስም የምትበረታው ሥጋ በደከመበት መስፈሪያ መጠን ነው።» በማለት ተናግሯል።

5/ ከዕለታት በአንድ ቀን አባ ዳንኤልና አባ አሞጽ አብረው በመንገድ ይጓዙ ነበር። በመንገዳቸው ላይ ሳሉ አባ አሞጽ «አባቴ! እኔና አንተ በአታችንን ዘግተን የምንቀመጠው መቼ ነው?» በማለት አባ ዳንኤልን ይጠይቀዋል።

አባ ዳንኤልም «እግዚአብሔር ከበአት ውስጥም ሆነ ከበአት ውጪ አለ። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ማን ሊለየን ይችላል?» በማለት ጥያቄውን በጥያቄው ውስጥ መልሷል።

6/ አባ ዳንኤል ሲናገር አባ አርሳኔምስ በሴቲስ ሳለ የመነኩሳቱን ንብረት የሚሰርቅ አንድ መነኩሴ ተነሥቶ ነበር።

አርሳኔሥ ይህን መነኩሴ ወደ በአቱ በመውሰድ ሊሸውዉና ለመነኰሳቱ ሰላማቸውን እንዲመልስላቸው ለማድረግ «አንተ አትስረት እንጂ እኔ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ እሰጥሃለሁ።።» ብሎ ነገረው። ከዚያም ወርቅ፣ ብር፣ ልብሶችና ሌላም የሚፈልጋቸውን ነገሮች ጨምሮ ይሰጠዋል። ከዚህም በኋላ መነኩሴው መስረቁን ይቀጥላል።

በዚህ ጊዜ እነዚያ አባቶች ተሰብስበው መነኩሴውን «አንድ ወንድም በድካሙ ምክንያት ኃጢአት ቢፈጽም ሊታገሡት ይቻላል፣ከሰረቀ ግን ነፍሱን ስለሚያውክና በአቅራቢያው የሚኖሩትን የወንድሞቹን ሰላም ስለሚያሳጣ ሊባረር ይገባዋል፤» በማለት ከገዳሙ ውስጥ አባርረውታል።

አባ ዮሐንስ አጭሩ (ዮሐንስ ሐጺር)

(ABBA JOHN THE DWRAF)

ዮሐንስ ሐጺር ከድሀ ወላጆቹ ቲስ በምትባል ቦታ ላይ የተወለደው በ339 ዓ.ም ነው። በአሥራ ስምንት ዓመቱ ከአባ አሞጽ አግር ሥር ተቀምጦ ለአሥራ ሁለት ዓመታት ያህል ይማር ዘንድ ወደ ሴቲስ ሄዷል። በበረሃ እያለ ከነበሩት የተለያዩ ባሕርያት መካከል ብዛት ያላቸው ደቀ መዛሙርትን ወደ እርሱ አቅርቦ ከለወጠ በኋላ በአቱን ለእነርሱ በመተው ብቸኝነቱን ላለማጣት ከዚያው ሥር ዋሻ ቆፍሮ በዚያ የመኖሩ ነገር ነው። ምንኩስናን ከተቀበለ በኋላ የተናገራቸው አባባሉቹ ጠቀሜታቸው የጎላ ስለ ነበር በተማሪዎቹ ተመዝግበውና ተጠብቀው ቆይተዋል። ከ407 ዓ.ም. በኋላ ወደ ሱኤዝ (Suez) እና ወደ እንጦንስ ተራራ ሄዶ ኖሯል።

1/ አባ ዮሐንስ ሐጺር የቴብስ (Thebes) ነዋሪ ከሆነ ከአንድ መነኩሴ ጋር ይኖር ዘንድ ከቤቱ ወጥቶ ወደ ሴቲስ በረሃ ሄዶ ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ይህ አባት አንዲት ደረቅ የዛፍ ቅርንጫፍ ከተከለ በኋላ ለዮሐንስ ሐጺር «ፍሬ እስክታፈራ ድረስ በየዕለቱ አንድ ቅል ሙሉ ውኃን አጠጣት!» አለው።

ውኃው ያለበት ቦታ እጅግ ሩቅ ስለ ነበር ዮሐንስ ሐጺር እዚያ ደርሶ የሚመለሰው ካለበት ሰፍራ መሸትሸት ሲል ተነሥቶ በማግስቱ ጠዋት ነበር። ከሦስት ዓመታት በኋላ ቅርንጫፏ ሰፊ ጸደቀች ፍሬ ሰጠች።

በዚህ ጊዜ ይህ አባት ጥቂት ፍሬዎችን ቆርጦ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመውሰድ በዚያ ላሉት መነኮሳት ወንድሞች «የመታዘዝን ፍሬ ተቀብሉኝና ብሉ!» በማለት አድሏቸዋል።

2/ በአንድ ወቅት አባ ዮሐንስ ሐጺር በአድሜ ታላላቆቹ ለሆኑ መነኮሳት፦ «ምንም ሌላ ሥራ ሳይሠሩ ለእግዚአብሔር ያለ ማቋረጥ ምስጋና እንደሚያቀርቡት ቅዱሳን መላእክት ያለ ምንም አሳብ በነጻነት ልኖር እፈልጋለሁ!» ይላቸዋል። ይሁን ከተናገረ በኋላ ካባውን አውልቆ ወደ በረሃ ወረደ።

ከአንድ ሳምንት በኋላ በአቱ ውስጥ አብሮት ወደሚኖረው መነኩሴ ወንድሙ ተመልሶ ይመጣል። ከዚያም ወንድሙ ያለበትን ቤት መዝጊያ ሲያንኳኳ እርሱ መዝጊያውን ከመክፈቱ በፊት «ማነው?» ብሎ ይጠይቃል።

ዮሐንስ ሐጺርም «እኔ ወንድምህ ዮሐንስ ነኝ!» ይለዋል።

ወንድሙም «ዮሐንስ መልአክ ስለሆነ በሰዎች ዘንድ የለም» ብሎ ይመልስለታል።

አባ ዮሐንስ ሐጺርም «አባክህ እኔ ነኝ!» በማለት በልመና ቃና እንዲከፍትለት መልሶ ይጠይቃል።

ከዚህ በኋላም ወንድሙ ሊያስገባው ፈቃደኛ ስላልሆነ ተስፋ ቆርጦ እስከ ጠዋት ድረስ በውጪ ይቆያል።

ጠዋት መዝጊያውን ከፍቶ ተመለከተውና «ሰው ስለሆንህ ለመብላት የግድ መሥራት አለብህ!» አለው።

ዮሐንስ ሐጺርም በእርሱ ፊት ተደፍቶ «ይቅርታ አድርግልኝ!» አለው።

3/ አንድ ጊዜ ዮሐንስ ሐጺር እንዲህ በማለት ተናገሮ ነበር፦

«አንድ ንጉሥ የጠላቶቹን ከተማ ለመያዝ ከፈለገ በመጀመሪያ ማድረግ ያለበት የጠላቶቹን የውኃና የምግብ መስመር ሙሉ ለሙሉ ማቋረጥ ነው። በዚህ ጊዜ ጠላቶቹ በውኃ ጥምና በረሃብ ስለሚደክሙ እጃቸውን ይሰጡታል። በሥጋም ቢሆን ልክ እንደዚሁ ነው። አንድ ሰው ሲጾም በጣም ስለሚርበው የነፍሱ ጠላቶች ፈጥነው ይደክማሉ።»

4/ «በአንድ ወቅት ጥቂት ገመዶች ተሸክሜ ወደ ሴቲስ አቅጣጫ ስጓዝ አንድ ግመሎችን የሚነዳ ሰው የማይገባ ነገር

ሲናገር ስሰማ ንዴት ስለ መጣብኝ ገመዶቼን ጥዬ ወደ መጣሁበት በሩጫ ተመልሼያለሁ!» በማለት ተናገር ነበር።

5/ በአንድ የመነር ወቅት በሥራ ላይ ሳለ አንድ ወንድም ባልንጀራውን በቁጣ ቃል ሲናገር ስለ ሰማ «እዚህም አለህ ማለት ነው?» በማለት ምርቱን ሳይሰበስብ ጥሎ ሸሽቷል።

6/ ሴቲስ ውስጥ ጥቂት መነኮሳት አባቶች ተሰብስበው ምግብ በመብላት ላይ ነበሩ። በእነርሱ መካከል አባ ዮሐንስ ሐጺር አብሯቸው ነበር። ምግቡን በመብላት ላይ እንዳሉ አንደኛው ብፁዕ አባት ተነሥተው ለሁሉም የሚጠጡትን ለማደል ሲሞክሩ ከዮሐንስ ሐጺር በስተቀር ሁሉም በአክብሮትና በትሕትና «አንቀበልምትም» አሏቸው።

በዚህ ጊዜ ሁሉም በአድናቆት ዮሐንስ ሐጺርን እየተመለከቱ «የሀላችን ታናሽ የሆንከው አንተ እንዴት በእኚህ ታላቅ አባት ልትገለገል ደፈርህ?» በማለት ይጠይቁታል።

አባ ዮሐንስ ሐጺርም:- «እኔ የሚጠጣ ለማደል ስነሣ ሁሉም ሲቀበሉኝ ዋጋዬን ስለማገኝ ደስ ይለኛል። አሁን የተቀበልከብት ምክንያት እርሳቸውን ሁላችንም አንቀበልምትም ስንላቸው ዋጋቸውን ስለሚያጡና በዚህ ምክንያት እንዳያዝኑ ስል እኔ ተቀብዬአቸዋለሁ።» ብሎ መለሰላቸው።

ይህን ሲሰሙ ሁሉም ስለማገናዘቡ በአድናቆት ተሞሉ።

7/ በአንድ ወቅት አባት አባ ዮሐንስ ሐጺር ከመነኮሳት ወንድሞቹ ጋር በቤተ ክርስቲያን አንባር ተቀምጦ ሳለ በሕሊናቸው ውስጥ ስላለ ነገር ያወሩታል።

በዚያው አካባቢ ሆኖ ይህን ሁኔታ በቅንዓት ዐይን ይመለከት የነበረ አንድ መነኩሴ ወደ ዮሐንስ ሐጺር ጠጋ ብሎ «ዮሐንስ! የምግብ ዕቃህ በመርዝ ተሞልቷል!» ይለዋል።

አባ ዮሐንስም መልሶ «አባ! ይህ ያልኸው ትክክል ነው። ይሁን እንጂ አንተ ይህን የተናገርኸው የዕቃውን ውጪ ብቻ ተመልክተህ ነው። የውስጡን ለመመልከት ብትችል ኖሮ ደግሞ ምን ልትል ትችል ነበር?» ብሎ መልሶለታል።

8/ አንድ ጊዜ በቅዳሴ ላይ ወንድሞች መነኩሳት ቅዱስ ቁርባን በተራ በመቀበል ላይ ሳሉ ከመካከላቸው አንደኛው ሲሰቅ የተመለከተው አባ ዮሐንስ እያለቀሰ፡- «ይህ ሰው ከልቡ ሊያለቅስ ሲገባው ሊያስቀው የቻለው በልቡ ውስጥ ምን ስላለ ነው?» በማለት ተናግሮ ነበር።

9/ ከዕለታት አንድ ቀን ጥቂት መነኩሳት «አባ ዮሐንስ ሐጺር አሳቡ ሲባክን በዚህ ዓለም ስላለ ነገር ሊናገር ስለሚችል ሂደን እንፈትነው!» ተባብለው ወደ እርሱ ይሄዳሉ።

ከዚያም፡- «በዚህ ዓመት በቂ ዝናብ ስለ ጣለና ዘምባባዎቹ ብዙ ውኃ ስለጠጡ ችግኞች ሊያወጡ ችለዋል። በዚህ ምክንያት

መንፈሳት ለእድ ሥራቸው የሚሆኑ በቂ የዘምባባ ቅጠሎች አግኝተዋል።» ብሎው ያወሩለታል።

አባ ዮሐንስ ሐጺርም «መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በሰዎች ልብ ውስጥ ስለ አደረና እንዲታደስ ስላደረገ እግዚአብሔርን ከመፍራት ይልቅ ትጠልን አስቀድመዋል ማለት ነው።» አላቸው።

10/ አንድ ቀን አባ ዮሐንስ ለሦስት ቅርጫቶች የሚሆን የዘምባባ ለሌን መታጠት ሲገባው ከፍተኛ መንፈሳዊ ተመስጠ ውስጥ ስለ ገቡና ሥራውን ስለ ዘነጋው የታታው ለሌን እድግ ስለ ረዘመ ከበእቱ ዘዳን በልጦ ቁልቁል ተመልሶ ወርዷል።

11/ አባ ዮሐንስ ሐጺር አንድ ቀን እንዲህ ብሎ ነበር፦

«እኔ ልክ ከትልቅ ዛፍ ሥር ተቀምጦ ሳለ ብዛት ያላቸው አውሬዎችና እባቦች ወደ እርሱ መጥተው ሊያጠቁት ሲሉ በፍጥነት ዛፉ ላይ ወጥቶ በማምለጥ የሚድን ሰውን አመስላለሁ። ምክንያቱም ይህ ሰው ፈጥኖ ዛፉ ላይ በመውጣት እንደ ዳነ ሁሉ እኔም በዛእቱ ውስጥ ተቀምጬ ሳለሁ ክፉ አሳቦች ሊዋጉኝ ፈጥኜ ወደ እግዚአብሔር በመጠጋት ከጠላቴ ስለማመልጥ ነው።»

12/ አባ ጴሜን (Poemen) ስለ አባ ዮሐንስ ሐጺር የተናገረው አለ። ከዕለታት አንድ ቀን ዮሐንስ ሐጺር በውስጡ ያለውን ስሜት እግዚአብሔር መሉ ለመሉ ከእርሱ እንዲያጠፋለትና ነጻ ሰው እንዲያደርገው ይጸልያል።

ከዚህ በኋላ ወደ እኔ መጥቶ «ራሴን ያለ ምንም ጠላት በሰላም ውስጥ አግኝቼዋለሁ!» ብሎ ነገረኝ።

አባ ጴሜንም «ዲድና እግዚአብሔር በአንተ ላይ ውጊያ እንዲከፈትብህ ያደርግ ዘንድ እነግሃለው። ከዚህ በኋላ ሊኖሩህ የሚገቡትን የመከራ ጊዜና ራስን ማዋረድ ለማግኘት ምክር። ምክንያቱም ነፍስ ዕድገት የምታመጣው በውጊያ ነው።» ብሎ ያሰናብተዋል።

ከዚህ በኋላ ውጊያው ሲመጣበት እግዚአብሔር ውጊያውን ከእርሱ እንዲይወሰድበት በጸሎት «ጌታዬ ሆይ! ከፈተና እንድወጣ አንተ ብርታቱን ስጠኝ!» ብሎ ጠየቀ።

13/ አንድ ጊዜ ደግሞ አባ ዮሐንስ ሐጺር እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

«ከዕለታት አንድ ቀን ሦስት መነኰሳት በባሕር ዳርቻ ቆመው ሳሉ 'የእሳት ክንፍ ተቀበሉና ወደ እኔ ኑ!' የሚል ድምፅ ከባሕሩ ማዶ መጣላቸው። በዚህ ጊዜ ሁለቱ በተሰጣቸው ክንፎች ባሕሩን ሲያቋርጡ አንደኛው ግን ክንፍ ሰላልተሰጠው ከመጠን በላይ እያለቀሰ በነበረበት ቦታ ይቀራል።

በመጨረሻ ግን ላልተሰጠውም ይሰጠዋል። ይሁን እንጂ ለእርሱ የተሰጠው ክንፍ የእሳት ሳይሆን ደካማና ኃይል የሌለው

ክንፍ ስለ ነበር አንዱ ባሕሩ ውስጥ እየገባ ሌላ ጊዜ ደግሞ በአየር ላይ እየተንሳፈፈ እንደ ምንም ብሎ ከባሕሩ ማዶ ይደርሳል::

በዚህ ትውልድም እንዲሁ ነው:: ለዚህ ትውልድ ክንፎች ከተሰጡት የሚሰጡት ደካማና ኃይል የሌሏቸው ክንፎች ናቸው::»

14/ አንድ መነኩሴ ወደ አባ ዮሐንስ ሐጺር ቀርቦ «ኦፍቢ እርሷ ራሷ በቁስል ተጎድታ ሳለ ባልንጀራዬን በመጻረር ስትናገር እንዴት አታፍርም?» ብሎ ጠየቀው::

በዚህ ጊዜ ዮሐንስ ሐጺር ከዚህ ሐሜት ጋር የሚዛመድ ተረት ለመነኩሴው ይነግረዋል:: እንዲህ እያለ:-

«አንዲት ሚስት የነበረችው አንድ ድሀ ሰው ነበረ:: ከጊዜ በኋላ ሌላ በጣም ቆንጆ ሴት ሰላየ እርሷንም ወደ እርሱ ያስገላታል:: በወቅቱ በአቅራቢያቸው በዓልና ድግስ ተደርጎ ስለ ነበር ሁለቱም ሴቶች ወደ በዓሉ ቦታ እንዲወስዳቸው ይለምኑታል:: ይሁን እንጂ በዚህ ሰዓት ግን ሁለቱም ዕርቃናቸውን ነበሩ:: ሁለቱንም ሚስቶቹን በርሜል ውስጥ ይከታቸውና በመርከብ አስሮና ወደ በዓሉ ቦታ ይወስዳቸዋል::

ዕለቱ ከፍተኛ መቀት ሲያመጣ በመርከቢቱ ተሳፍረው የመጡት ሰዎች ሁሉ ስለ ደከማቸው ባሉበት ቦታ ሳያንቀላፉ ጋደም - ጋደም ይላሉ::

በበርሜል ውስጥ ከነበሩት ሌቦች መካከል አንደኛዋ ተስ ብላ ከውጣች በኋላ አካባቢው ላይ ተከምሮ ከነበረው ቆሻሻ ውስጥ ከተጣሉት በተቀዳ ጨርቆች መካከል የሚበቃትን በዘዴ እንደ ነገሩ በማያያዝ ለራሷ ቀሚስ ታበጃለች። ከዚያም ያለ ዕፍረት በሙሉ ልብ በሕዝቡ መካከል ትራመድ ጀመር።

ሌላዋ በበርሜሉ ውስጥ እርቃኗን የተቀመጠችው ሴት ለባሏ «ይህቺን ያለ ምንም ዕፍረት ዕርቃኗን በሕዝቡ መካከል የምትመላለሰው ዘማዊት ሴትህን ተመለከትካት?» ብላ ትጠይቀዋለች።

በዚህ ንግግሯ በጣም ያዘነባት ባሏ እንዲህ ይላታል፦ «እርሷ በጣም ጥሩ ዘዴ ዘይዳለች፣ ሌላው ቢቀር እንደ ምንም ብላ ከፊል እርቃኗን ሸፍናለች፣ አንቺ ግን ሙሉ ለሙሉ ዕርቃንሽን ነው ያለሽው፣ እና እንዲህ ያለውን ነገር ለመናገር ጥቂት እንኳ አታፍሪም?፣» አላት።

ስለ ባልንጀራው መልካም የማይናገረው ሰውም ልክ እንደዚህች ሴት ያለ ሰው ነው።»

15/ ለመለወጥ ጥረት ስለምታደርግ ነፍስ አባ ዮሐንስ ሐጺር ለአንድ መነኩሴ ያስተማረበት ምሳሌ እንደሚከተለው ተጽፎ ይገኛል።

«በክብሩማ መነገል ብዙ ወዳጆች ያሏት አንዲት ቆንጆ ሴተኛ አዳሪ ነበረች። የከተማዋ ከንቲባ ወደ እርሷ ቀርቦ 'መልካም ሌት እንደምትሆኚ ቃል ከገባሽልኝ አሁኑኑ አገባሻለሁ' ይላታል። እርሷም በአሳቡ ተስማምታ ቃል ስለ ገባችለት ወደ ቤቱ ይዟት ሄደ።

ወዳጆቿ ድጋሚ ሲያገኟት ስለ ፊለገ፡ እርስ በእርሳቸው እንዲህ እያሉ ይመካከሩ ጀመር፡- 'የከተማው ከንቲባ ወዳጃችንን ወደ ቤቱ ወስዷታል። በግልጽ ወደ ቤቱ ከሄድን ጉዳያችንን ስለማ.ያውቅብንና ስለሚያስፈርድብን በቤቱ ጓሮ ዞረን እናፏጭላት። የፋጨቶቻችንን ድምፅ ለይታ ስለምታውቃቸው ከቤቷ ወርዳ ትመጣለች። ለማንኛውም ግን እርሷ ትምጣልን እንጂ እኛ አንጣላም!' አሉ።

በመጨረሻ እንደ ተመካከሩት በቤቱ ጓሮ ዞረው ሲያፏጩላት ጆሮዋቿ ቆሙ። ይሁን እንጂ ወደ እነርሱ ልትወርድ ስላልፈለገች ፊጠን ብላ ወደ እንግዳ መቀበያው አዳራሽ ገባችና በሮቹን ዘጋግታ ከውስጥ ተቀመጠች።

ልክ እንደነዚሁ ነፍሳችን በነዚህች ሴት ስትመሰል ወዳጆቿ ደግሞ በምኞቶቻችን ይመሰላሉ። ከንቲባው የሚመሰለው በምንወደው በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በቤቱ ውስጥ ያለው እንግዳ መቀበያ አዳራሽ በዘላለማዊ ቤታችን ወይም በመንግሥተ ሰማያት ሲመሰል የሚያፏጩት ሰዎች ደግሞ በርኩሳን መናፍስት ይመሰላሉ። በመጨረሻም ይህ ምሳሌ ነፍሳችን ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር ከተጠጋች በእርሱ ኃይል እንደምትድን ያስረዳናል።»

16/ በአንድ ወቅት አባ ዮሐንስ ሐጺርና ጥቂት መነኰሳት ወንድሞቹ ወደ ሴቲስ በመንዝ ላይ እንዳሉ ጊዜው ስለ መሸባቸው የሚመራቸው ሰው አቅጣጫውን ስለ ሳተ መንገዱ ይጠፋበታል።

መነኰሳቱም የመጥፋታቸውን ነገር ለአባ ዮሐንስ በመንገር «አባ! የሚመራን ወንድማችን መንገዱ ስለ ጠፋው እንዲሁ ስንባዝን ሞተን ማደራችን ነውና ምን ብናደርግ ነው የሚሻለን?» ብለው ይጠይቁታል።

አባ ዮሐንስ ሐጺርም «ወንድማችንን በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ብናናግረው በድንጋጤ፣ በጉዘንና በእፍረት ሊሞላ ይችላል። ስለዚህ እኔ የታመምኩ በመምሰል ከዚህ በላይ መራመድ አልችልም ብዬ እቀመጣለሁ። ከዚህ በኋላ ሁላችንም እስኪነጋ ድረስ ምሽቱን እዚህ እናሳልፋለን።» ይላቸዋል።

ልክ አባ ይህን ሲያደርግ መነኰሳቱም «እኛም ትተንህ ልንሄድ ስለማንችል ከአንተ ጋር እዚሁ አብረንህ እናድራለን!» አሉት።

በዚህ ዓይነት መንገድ እዚያው ቁጭ ብለው ስለ አደሩ ወንድማቸውን ሳያሳዝኑት ቀሩ።

17/ ሴቲስ ውስጥ ራሱን የጣለ ነገር ግን ሕሊናው ያስቸገረው አንድ መነኩሴ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ይህ አባት ስለ መርሳት አንዳንድ ነገሮችን ይጠይቀው ዘንድ ወደ አባ ዮሐንስ

ሐጺር ሄደ። አባ ዮሐንስ ሐጺርም አንዲት ቃል ነገረውና ወደ በአቱ አሰናበተው።

መነኩሴው በአቱ መግቢያ ላይ ሲደርስ ዮሐንስ ሐጺር የነገረውን ቃል ይረሳዋል። ተመልሶ ወደ እርሱ ሲመጣ ያችኑ ቃል መልሶ ይነግረዋል። አሁን በአቱ ደጃፍ ላይ ሲደርስ የተነገረችውን ቃል ይረሳል። ይህንን ተመላሳይና ተደጋጋሚ ምልልስ ቢያደርግም መነኩሴው ዝንጉ በመሆኑ የተባለውን ሊፈጽም አልቻለም።

በመጨረሻ መነኩሴው አባት ከአባ ዮሐንስ ሐጺር ጋር ሲገናኝ፡- «ታውቃለህ አባ!? አሁንም በመጨረሻ የነገርኸኝን ቃል ረስቼዋለሁ! ስለዚህ ከዚህ በላይ በመመላለስ አንተን ማድከም ስለ ከበደብኝ በዚያው ቀርቼያለሁ።» አለው።

ዮሐንስ ሐጺርም «አንድ ሻማ ለክ-ስ!» አለው።

መነኩሴው የታዘዘውን አደረገ።

አባ ሐጺር ቀጠል አድርጎ «ሌሎች ሻማዎችም አምጣና እንደ መጀመሪያው ሻማ ለክ-ሳቸው!» ብሎ ሲነግረው መነኩሴው አሁንም እንደታዘዘው ይፈጽማል።

ከዚህ በኋላ አባ ዮሐንስ ሐጺር መነኩሴውን፡- «ሌሎቹ ሻማዎች ስለ ተለኮሱ በመጀመሪያ በተለኮሰው ሻማ ላይ ምን የሚያመጡት ተጽእኖ አለ?» ብሎ ጠየቀው።